# አብዮታዊት ኢትዮጵያ

፱




ጳጉሜን ፭ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ.ም.

## ለውይይት መነሻ

አብዮታዊት ኢትዮጵያ ከቍጥር ፬ ጀምራ «ለነማርክስ ፍልስፍና አጭር መግቢያ» በሚል ርእስ ሥር በተከታታይ ትምህርታዊ የሆኑ የፍልስፍና ጽሑፎች ታቀርባለች ። እነዚህ ጽሑፎች የማርክሲዝምን ርእዮተ ዓለም ገና ለመጀመሪያ ጊዜ ለሚተዋወቁ የውይይት ክበቦች መነሻ ሃሳቦች እንደሚሰጡ ሆነው የቀረቡ ናቸው ።

# የኅብረተሰቦች አስተዳደግ

( ካለፈው የቀጠለ )

እስካሁን ድረስ የማርክሲሳዊ ፍልስፍናን ዋና ዋና ሐሳቦች ምን እንደሆኑ በአጠቃላይ ተመልክተን እንቅስቃሴ የጠቅላላው ቁስ አካል ባሕሪ መሆኑን ፤ ለውጥም ሲባል የሚነሣባቸውን ምክንያቶችና እንዴት እንደሚካሄድ አቅጣጫውን በአጠቃላይ ተመለከትን ። የማርክሲሳዊ ፍልስፍና ዲያሌክቲካዊ እንደመሆኑ መጠን የኅብረተሰቦችንም ታሪክ መለዋወጥ የሚመለከተው በዚሁ የእንቅስቃሴዎች ሁሉ ሕግ በሆነው በዲያሌክቲክስ እየተጠቀመ መሆኑን አየን ። የማርክሲሳዊ ፍልስፍና ቁስ አካላዊ እንደመሆኑ መጠን ኅብረተ ሰብንም ሲመረምር ቁስ አካልን ከሐሳብ እያስቀደመ መሆኑን ተመለከትን ።

የማንኛውንም ኅብረተሰብና የታሪክ ለውጥ መመልከት የሚቻለው እነዚህን መሠረታዊ መርሆች በመከተል ብቻ ነው ። በነዚህ መሠረታዊ መርሆች ካልተመራንና እነሱን ተመርኩዘን ካልተመራመርን ስለኅብረተሰባችን ፤ ስለታሪክ ለውጥ ስለአብዮትና ስለመደቦች ትግል ምንነት በፍጹም ልንረዳ አንችልም ።

ማንኛውንም ኅብረተሰብ በምናጠናበት ጊዜ በቅድሚያ መነሻችን መሆን ያለበት አንድ ነገር አለ ። ይኸውም ኅብረተሰቡ የቆመበት መሠረት ነው ። ሰዎች ለመኖር እንዲችሉ ማለትም ለመብላት ፤ ለመጠጣት ፤ ለመልበስ ፤ ለመጠለል . . . ወዘተ የሚበላ ፤ የሚጠጣ ፤ የሚለበስና ለመጠለያ የሚሆናቸውንም መሥራት አለባቸው ። ይህም ማለት የሰዎች ኑሮ መሠረቱ ሥራ ነው ማለት ነው ። ሰው ለመኖር ማምረት አለበት ። ይህ የምርት ሥራ ቢያንስ በሦስት አንፃሮች የኅብረተሰብ ሕልውናና የእድገቱ መሠረት ነው ማለት ይቻላል ። ይኸውም እንደሚከተለው ነው ።

፩ኛ ትምህርት—ከን- ዓ-

፩ኛ በመጀመሪያ ደረጃ ሰውን ሰው የሚያሰኘው የህልውናውና የሰውነቱ የራሱ ምልክቱ ለእንጀራው ሲል መውጣት መውረዱና ማምረት መቻሉ ነው ማርክስና ኤንግልስ ስለጥንት ሰዎች አንስተው የሰው ዘር ከእንስሳት መለየት ስለጀመረበት ሁኔታ ሲያስረዱ እንዲህ ብለዋል ። «እነዚህን ግለሰቦች ከእንስሳት የለያቸው የመጀመሪያው ነገር ማሰብ መቻላቸው አይደለም ። ለኑሮዋቸው የሚያስፈልጋቸውን ማምረት መጀመራቸው ነው እንጂ » ።

ሰው ከእንስሳት ዓለም የሚለይበትን ሁኔታ ተንትነው ሲያስረዱ እነዚህ የሳይንሳዊ ሶሻሊዝም አስተማሪዎች በዚህ ሽግግር ጊዜ የምርት ሥራ የተጫወተውን ሚና በደንብ አድርገው አብራርተዋል ።

በግምት ከአምስት ሚሊዮን ዓመት በፊት እጅግ ከፍተኛ የአየር ጠባይ ለውጥ ስለመጣ በብዙ የዓለም ክፍሎች ይገኙ የነበሩ ታላላቅ ጫካዎች ወደሙ ። በነዚህ ጫካዎች ዛፍ ላይ ኑሮዋቸውን የመሠረቱ ሁሉ መሬት ወርደው አዲስና አስቸጋሪ ኑሮ ለመኖር ተገደዱ ። መሬትም መውረድ ብቻ ሳይሆን ከቀድሞው የተለየ የምግብ ዓይነት መልመድ አለበለዚያም መጥፋት ሆነና አብዛኞቹ ይህንን ለውጥ መቋቋም አቅቷቸው ከምድረ ገጽ ጠፉ ። ከነዚህ ከቀድሞ ጫካ ኗሪዎች ውስጥ አንድ የዝንጀሮ ዘር እንደምንም ብሎ በማደንና ሌሎች እንስሳትን በመብላት የህልውናው ምንጭ ለማድረግ ቻለ ። ይህንን ለማድረግም የአደን መሣሪያዎች ብቻ ሳይሆን ከመሰሎቹ ጋር አብሮና ተጋግዞ ማደንም አስፈለገው ። በየጊዜው ማደን ማለት በየጊዜው የአደን መሣሪያዎች መሥራትን የሚጠይቅ ነገር ነበር ። ይህም ማለት እነዚህን የአደን መሣሪያዎችን ለመሥራት የተለዩ ዕቃዎች መሥራት ለምሳሌ እንጨት ማሾል ድንጋይ መጥረብ አስፈለገ ። ይህንን ዛሬ የሰው ዘር መንኰራኵሮችን እየሠራ ወደጠፈር በሚመጥቅበት የሳይንስ ዘመን እንደቀላል ነገር አድርገን እንወስዳቸው ይሆናል ። ነገር ግን ይህ ወቅት በሰው ዘርና በእንስሳት መካከል የቆመ አዋሳኝ ምዕራፍ ነበር ። ሰው ከእንስሳት የተለየበትና ኑሮውን በየጊዜው እያሻሻለ ከዚህ ለመድረስ የበቃው ለኑሮው የሚያስፈልጉትን ዕቃዎች ከላይ በጠቀስነው ሁኔታ መሥራት በጀመረ ጊዜ ነው ።

ሰውን ከእንስሳት የሚለየው ምንድን ነው ? እንስሳትና ሰውን በዚህ በኩል ብናነጻጽራቸው ለህልውናቸው የሚያደርጉት ትግል በተለያዩ ደረጃዎች ላይ መሆናቸውን እንረዳለን ።

**የእንስሳት የኑሮ ትግል**

፩. ለአደን ይወጣሉ

፪. ያገኙትን ደካማ እንስሳ ያለምንም መሣሪያ ይይዛሉ ።

፫. የያዙትን እንዳለ ( ጥሬውን ) ይበላሉ ።

**የሰው ዘር የኑሮ ትግል**

፩. የድንጋይ መጥረቢያ ይሠራል

፪. በዚህ መሣሪያ ጦር ያሾላል ።

፫. ለአደን ይወጣል

፬. ያገኘውን እንስሳ በጦሩ ይገድላል ።

፭. የገደለውን እንስሳ በእሳት ቀቅሎ ይበላል ።

ማምረት መጀመር ሰውን ከሌሎች እንስሳት በመለየት ብቻ አልተወሰነም ። ከዚያም አልፎ ሰው ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የምርት ሥራውን የሚያካሂደው ከመሰሉ ከሰው ጋር በመሆኑ ለማምረት መነጋገር አስፈላጊ ስለሆነ ቋንቋም ከምርት ጋር ቀስ በቀስ እየተፈጠረና እየዳበረ መጣ ። በዚህ ሁሉ የተነሣ ነው ሠርቶ ማምረት ሰውን ሰው ማድረግ ብቻ ሳይሆን የሰዎች የኅብረተሰብ እድገትና አንቀሳቃሽ መሠረት ነው የሚባለው ።

ማርክስ የሰው ዘር በፖለቲካ በሳይንስ በሃይማኖት ከመራቀቁ በፊት መብላት መጠጣት ። መልበስ ፤ መጠለል እንዳለበትና ለዚህ ደግሞ ሠርቶ ማምረት እንደሚያስፈልገው ያስረዳል ። እንግዲህ ሠርቶ ማምረት የማንኛውም ኅብረተሰብ መሠረት ነው ማለት ነው ።

## ፪ኛ ሠርቶ ማምረት የኅብረተሰቡ መሠረት

ሰዎች ለመኖር አስቀድሞ ሠርተው ማምረት አለባቸው ። ምርት ከሌለ ሕይወት የለም ። ሰው የለም ። ኅብረተሰብ የለም ። በዓለም ላይ በአሁኑ ወቅት የተለያየ ኑሮ የሚኖሩ አገሮችና ሕዝቦች አሉ ። እነዚህ አገሮች በአስተሳሰብ ፤ በመንግሥት ዓይነት ፤ በባህል ፤ . . . የተለያዩ ናቸው ። ነገር ግን ምንም የተለያዩ ቢሆኑ ኅብረተሰቦችን ሁሉ አንድ የሚያደርጋቸው ነገር አለ ። ሁሉም ለመኖር እየሠሩ ያመርታሉ ። ታዲያ ሁሉ ሠርቶ አምራች ከሆነ ከላይ የጠቀስናቸውና ሌሎችም ልዩነቶች ከየት ይፈልቃሉ? አንዱ እጅግ የተራመደ ሌላው እጅግ ወደ ኋላ የቀረ ለምን ሆነ? በአንዱ ኅብረተሰብ ፍትሕና ነፃነት ሲኖር በሌላው ለምን ጭቆናና ብዝበዛ ይነግሣል ? የዚህ መሰበጣጠር መሠረታዊ ምክንያት እነዚህ የተለያዩ አገሮች ሠርተው የሚያመርቱበት ስልት የተሰበጣጠሩ በመሆናቸው ነው ።

ኢትዮጵያን ከአሜሪካንም ሆነ ከሶቪዬት ኅብረት የሚለያት ዋናው ምክንያት በኢትዮጵያ ተንሰራፍቶ የቆየው ስልተ ምርት በነዚህ ሁለት ሀገሮች ካለው ስልተምርት የተለየ በመሆኑ ነው ። ማርክሲዝም በዚህ በኩል ያለው አቋም ግልጽ ነው የአንድን አገር ርምጃ የሚገታው ወይም የሚያፋጥነው ከዚህም ጋር አያይዞ ባህሉን ፤ ሃይማኖቱን ፤ የመንግሥቱን ዓይነት . . . የሚወስነው ዋና ነገር ይኸ አገር የቆመበት የሠርቶ ማምረት ስልቱ ነው ።

ይህንን ዝቅ ብለን በዝርዝር እንመለከታለን ። ሕዝቦችንና አገሮችን የተለያዩ የሚያደርጋቸው የቆሙበት ስልተ ምርት ነው ሲባል ዋናውንና ወሳኙ የሆነውን ምክንያት ለመጠቆም ያህል እንጂ ይኸ ብቻ በቂ ነው ለማለት አይደለም ። የአንድ ሀገር የጂኦግራፊ አቀማመጥም ሆነ የሕዝብ ብዛት ወይም ማነስ እንደሁኔታው የሀገሩን ዕድገት ሊያፋጥን ወይም ሊገታ ይችላል ።

ለምሳሌ የተፈጥሮ አቀማመጥን እንውሰድ ፤ ሰው ሠርቶ ለማምረት በአካባቢው ባለው የአየር ጠባይ የመሬት ልማት ፤ የማዕድን ሀብት ፤ . . . እነዚህን በመሳሰሉ ሁሉ የግድ መጠቀም አለበት ። እነዚህ

በብዛት ከተገኙ ሰው ለእንጀራ የሚያደርገው ትግል በዚያው ልክ የተመቸ ይሆናል ። እነዚህ ደግሞ ካልተገኙ ሰው ለእንጀራው የሚያደርገው ትግል የዚያኑ ያህል አደጋችና አድካሚ ይሆናል ። ይህ ምንም የሚያከራክር ጉዳይ አይደለም ። ይሁን እንጂ የአንድን አገር እድገት የሚገታው ወይም የሚያፋጥነው ዋናውና ወሳኙ የተፈጥሮ አቀማመጡ ነው ወይ? የለም ይኸ ዋናው ምክንያት አይደለም ለምሳሌ ሀገራችን ተራሮቿ ወንዞቿ የአየሯ ጠባይ . . . ያው የቀድሞው ነው ። አልተለወጠም ። በዚህ የተፈጥሮ ሀብቷ እጅግ የታደለች ሆና ግን እጅግ ወደ ኋላ የቀረች ናት ለምን ? ይህንንም ዝቅ ብለን እንመለከታለን ። በአሁኑ ጊዜ የመሳፍንቱ ሥርዓት እየፈራረሰ አዲስ ሥርዓተ ማኅበር በመገንባት ላይ ነው ። ትግሉ እንደዚህ ቀጥሎ ኅብረተሰባዊት ኢትዮጵያ በምትገነባበት ጊዜም ተራሮቿ ወንዞቿ የአየሯ ጠባይ በተራቀቀ ሳይንስ ለሕዝቧ ጥቅም እንዲውሉ ይደረጋሉ እንጂ መኖራቸው አይቀርም ።

ሀገሪቱ ያላት የሰው ሀብትስ ? የሕዝቧ ማነስ ወይም መብዛት መጣበብ ወይም ተስፋፍቶ መኖር የሀገሪቷን ዕድገት ሊገታ ወይም ሊያፋጥን አይችልም ወይ ? መቸም አገር ያነሰው የለም ። ሠርቶ ለማምረት የሰው ጉልበትና ዕውቀት ያስፈልጋል ። የሰው ቍጥር ልከኛ መሆን ለሀገር እድገት ሲስማማ የሰው ማነስ ወይም መብዛት ደግሞ እንደሁኔታው የሀገሪቱን እድገት ሊገታ ይችላል ። ይሁን እንጂ እዚህም ላይ ከፍ ብለን እንዳልነው ነው ። የአንድ ሀገር መደየት ወይም መበልጸግ ፤ ወደ ኋላ ወይም መራመድ የሚወስነው መሠረታዊ ነገር የሕዝቧ ቍጥር አይደለም ። ቻይና አብዮቷን ከማካሄዷ በፊት በፊውዳሊዝምና በኢምፔሪያሊዝም ጨለማ ውስጥ የምትዳክር አገር ነበረች ። በዚያን ጊዜ አብዮታውያን የቻይና ሕዝብ ችግር ረኃብ ፤ መራቆት ፤ የመጣው በነዚሁ ጥንድ ጠላቶች መዘዝ ነውና እነሱን እንደምስስ ብለው ይታገሉ ነበር ። ኢምፔሪያሊስቶችም ፤ ሌሎችም የከበርቴ «አዋቂዎች» ነን የሚሉት ግን የቻይና ችግርና መሠረቱ የሕዝቡ መብዛት ነው ብለው ትግሉን የተሳሳተ አቅጣጫ ለመስጠት ይሞክሩ ነበር ። አሁን ከአብዮቱ ወዲህ የቻይና ሕዝብ ቍጥር ጨምሮ እንዲያውም ከ፰፻ ሚሊዮን በላይ ሆነዋል ። እንደከበርቴዎች አዋቂዎች» ቢሆን ኖሮ ቻይና ሕዝቧ ስለ ጨመረ ጨርሶ የማትወጣበት ማጥ ውስጥ ገብታ ነበር ማለት ነው ። እንደምናየው ግን ይቺ አገር የቀድሞውን ረኃብ ሙሉ በሙሉ አስወግዳ አዲስ ሥርዓት በመገንባት ላይ ትገኛለች ። ስለዚህ የሕዝብ ቍጥር እርግጥ በአንድ አገር እድገት ላይ ተጽእኖ ቢኖረውም ዋናው እሱ አይደለም ።

ታዲያስ እንግዲህ የአንድን አገር የእድገት ርምጃ የሚወስነው ፤ የሚያንቀሳቅሰው ወይም የሚገታው ዋና ኃይል ምንድን ነው ይህንን ከላይ ጠቀስ አድርገነዋል ። የማንም ኅብረተሰብ የቆመበት መሠረት ሠርቶ የሚያመርተው ሀብት ነው ። ስለዚህም ሀብቱ ፤ ብልጽግናው ወደኋላ መቅረቱ ፤ በእውቀት መበልጸጉ ፤ በጤና መታወኩ ይህን ሁሉ የሚወስነው የሥራው ፍሬ በርካታ ወይም አነስተኛ ፤ መሆኑ ነው ። ይህም ራሱ የሚወስነው በማሣሪያው ጥራት ፤ በእውቀቱ መዳበር ፤ በሳይንስ መራቀቅ እንደሆነ ግልጽ ነው ። ግን ደግሞ ሌላ ነገርም አለ ። የመሣሪያው መራቀቅም ሆነ የምርቱ መበርከት ብቻውን አንድ አገር የደረሰችባትን የሥልጣኔ ደረጃ አያመለክትም ። ይህንንም ደረጃ ለመለካት ሰዎች ከመሰሎቻቸው ጋር እንዴት እንደሚሠሩና ከዚህም ሠርተው ያገኙትን በርካታም ሆነ አነስተኛ ምርት እንዴት እንደሚከፋፈሉ ማየትም ያስፈልጋል ። እንግዲህ የኅብረተሰብ መሠረት ሠርቶ ማምረት ነው ። ሲባል የሚወስነውም ኅብረተሰቡ ባለው የማምረቻ ኃይልና በሰዎች ባለውም የሥራ ግንኙነት ነው ማለት ነው ።

በዚህ አንፃር ስናየው እያንዳንዱ ሀገር የራሱ የሆነ የሠርቶ ማምረት ዘዴ ስላለው ለምሳሌ በዓለም ፩፻፶ አገሮች ይኖሩ እንደሆነ ፩፻፶ ዓይነት ስልተ ምርቶች አሉ ማለት ያሰኛል ። ግን አይደለም እንኳን አሁን ይቅርና የሰው ልጅ በኅብረተሰብ መኖር ከጀመረበት ወቅት አንስቶ እየተነሡ እያደጉና እየፈረሱ የተቀያየሩት ዋና ዋና ስልተ ምርቶች ፭ ዓይነት ብቻ ናቸው ። እነሱም የጋርዮሽ ዘመን ስልተ ምርት ፤ የባርያ ዘመን ስልተ ምርት፤ የፊውዳል ዘመን ስልተ ምርት ፤ የካፒታሊስት ዘመን ስልተ ምርትና የሶሻሊስት ዘመን ስልተ ምርት ናቸው ። እነዚህ ውስጥ ከመግባታችን በፊት ግን በቅድሚያ ስልተምርት ማለት ምን እንደ ሆነ እናብራራ ።



## ፫ኛ ስልተ ምርት የምርት ኃይሎችና የምርት ግንኙነቶች

አርሶ ለማምረት እንዲቻል የግድ ሞፈር ፤ ቀንበርና በሬ እንዲሁም የሰው ጉልበትና ዕውቀት ያስፈልጋል ። መሬት ፤ ፋብሪካ ፤ መኪና . . . ወዘተ ይህንን የመሳሰሉ ሁሉ ለማምረት የግድ የሚያስፈልጉ ነገሮች ናቸው ። እነዚህም የምርት መሣሪያዎች ይባላሉ ። ነገር ግን እነዚህ መሣሪያዎች ብቻቸውን ምንም መሥራት አይችሉም ። የግድ የሰው ጉልበት ያስፈልጋል ። ይህም ደግሞ የሰው ጉልበትንና ዕውቀትን ይጠይቃል ። ምርቱን ለማሳደግ መልክ ለማስያዝና ከጥቅም ላይ ለማዋል የሚችለው ሰው ነው ። እንግዲህ እነዚህ ሁለቱ ሲጣመሩ የምርት ኃይሎች ይባላሉ ።

ግን ሠርቶ ለማምረት መሣሪያ ፤ የሰው ጉልበትና ዕውቀት መገናኘታቸው ብቻ አይበቃም ። የዚያኑ ያህል የሥራን ውጤት የሚወስንና የአገሪቱን የእድገት ደረጃ የሚያሳይ በሰዎች መሐከል ያለው የሥራ ግንኙነት ነው ። እነዚህም ደግሞ የምርት ግንኙነቶች የምንላቸው ናቸው ። እነዚህም ለምሳሌ እኩል በሆኑ ሰዎች ወይም ደግሞ በባሪያና በባሪያ ፈንጋይ ፤ በባለርስትና በጪሰኛ ፤ በቡርዥዋና በወዝአደር መሐከል ያሉት የተለያዩ ግንኙነቶች ናቸው ። እነዚህ የተለያዩ ግንኙነቶች በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ሊከፈሉ ይችላሉ ። በእኩልነት ላይ የተመሠረቱ የምርት ግንኙነቶች ሊኖሩ ይችላሉ ። ወይም ደግሞ በበዝባዥና በተበዝባዥ መሀከል ያሉ የምርት ግንኙነቶች ሊሆኑ ይችላሉ ። ይህ ሊወሰን የሚችለው ከላይ የጠቀስናቸው የምርት መሣሪያዎች በማን እጅ እንደሆኑ እየታየ ነው ። እነዚህ መሣሪያዎች ማለትም ፋብሪካው ፤ መሬቱ ፤ ገንዘቡ የግል ከሆኑ በሰዎች መሐከል የሚፈጠረው ግንኙነት የአራሽና የአሳራሽ ፤ የሠሪና የአሠሪ የበዝባዥና የተበዝባዥ ግንኙነት ይሆናል ። ብዝበዛ ስላለ ክፍያው ላይ ባለቤት የሆነ ፤ ብዙ የሚሠራ ደግሞ ትንሽ ይወስዳል ። በሌላ በኩል ደግሞ የምርት መሣሪያዎች የጋራ ከሆኑ የምርት ግንኙነቶችም በእኩልነት ላይ የተመሠረቱ ይሆናሉ ። እንደዚህም ስለሆነ የምርቱ ክፍያ በሚመጣበትም ጊዜ ለሁሉም የሥራው ዋጋ ይከፈለዋል ። ባጭሩ የምርት ግንኙነቶች የሚወሰኑት በምርት መሣሪያዎች ባለቤትነትና በምርት ክፍፍል ድርሻ እየታየ ነው ማለት ነው ።

እንግዲህ ስልተ ምርት የሚባለው የአንድን አገር ወይም ኅብረተሰብ የምርት ኃይሎች ብቻ ሳይሆን ከነዚሁ ጋር ተያይዞ የሚገኘውን የምርት ግንኙነትም አዋህዶ የያዘ የሠርቶ ማምረትና የኑሮ ዘዴ ነው ማለት ነው ።

ማምረት የማንኛውም ኅብረተሰብ የኑሮ መሠረት መሆኑን ከፍ ብለን ገልጸናል ። የሰው ልጅ የሥራ ፍሬ ከዓመት ዓመት እየተሻሻለና እያደገ፤ ያለማቋረጥ ከፍ ከፍ የሚል መሆኑን የማንኛውም ኅብረተሰብ ታሪክ እየደጋገመ የሚያሳየው የተፈጥሮ ሕግ ነው ። የሰው ፍላጐቱ ከቀን ቀን እያደገ ፤ እየተሰበጣጠረና እየተራቀቀ ይሄዳል ። በዚሁ ልክ ደግሞ የሥራው ዓይነት እየተሰበጣጠረና እየተራቀቀ መሔዱ የሚያስገርም አይደለም ። የሰውን ልጅ እያደገ የመሔድ ፍላጐት ለማርካት ሰው የሥራውን ፍሬ በየጊዜው በርካታ እያደረገ ለመሔድ ፤ ስለዚህም መሣሪያውን ማሻሻልና ማራቀቅ ፤ ዕውቀትን ማስፋፋት ይኖርበታል ።

ሰው ለመኖር ሠርቶ ማምረት ብቻ አይበቃውም ። የግድ ያለማቋረጥ የሚያድግ ፍላጐቱን ለማርካት ምርቱንም ማሳደግ አለበት ። ይኸውም የማይለወጥ የሕይወት ሕግ ነው ። እንዲያውም የኅብረተሰብ ታሪክ ዋና ይዘት የዚህ ንጉሥ መውጣት ወይም የዚያ ንጉሥ መውረድ ፤ የዚህ ጀግና ወይም የዚያ ፈሪ ድርጊቶች ጥርቅም ሳይሆን የዚህ የኅብረተሰቡን ምርት ያለማቋረጥ ለማሳደግ የሚደረገው የማምረት ትግል ታሪክ ነው ። የአንድ ሀገር ወይም ኅብረተሰብ ታሪክ የማይቀረውና የማያቋርጠው የምርት መሻሻልና ማደግ ታሪክ ነው ለማለት ይቻላል ።

ከላይ እንዳየነው ሠርቶ ለማምረት ማንኛውም ኅብረተሰብ የራሱ የሆነ ስልተ ምርት አለው ። አንድ ዓይነት ስልተ ምርት ላይ ተመሥርቶ ከቆየ፤ ያንን ሳይለውጥ ያንን ሳያሻሽል ኑሮውን ያለማቋረጥ ማሳደግ አይችልም ። የኢትዮጵያ ገበሬ ለምሳሌ ኑሮውን ለማሻሻል ከፈለገ ከሞፈርና ቀንበር

ተላቆ ወደዘመናዊ እርሻ መስማራት ይኖርበታል። ነገር ግን ይህ ስልተምርት የግድ መለወጥ አለበት ስንል ምን ማለታችን ነው ? ከላይ ስልተምርት የሚባለው የምርት ኃይሎችንና የምርት ግንኙነቶችን አጣምሮ የያዘ ነው ብለናል ። ስለዚህ ስልተ ምርት እንዲሻሻል ፣ ምርት እንዲያድግ የምርት ኃይሎች ማለትም መሣሪያው የሰው ዕውቀት ብልሀት ጉልበት . . . መሻሻል አለባቸው ። ግን ደግሞ እነዚህ ብቻቸውን ስለተሻሻሉ ስልተምርቱ ተለወጠ ማለት አይቻልም ። ለዚህ የግድ የምርት ግንኙነቶችም መሻሻል አለባቸው ። ይህ ደግሞ የማይቀር የተፈጥሮ ሕግ ነው ። የምርት ኃይሎች እያደጉ ከሔዱ የምርት ግንኙነቶችም የግድ ተለውጠው ለጊዜውና የምርት ኃይሎች ለደረሱበት ደረጃ የሚስማሙ ሆነው መገኘት አለባቸው ።

የዚህ የስልተ ምርት መለዋወጥና የአንድ ሀገር ከአንድ ዓይነት ሥርዓት ወደሌላ ዓይነት ሥርዓት መሸጋገር የሚካሄደው እንዴት ነው ? ሁሉቱም ተያይዘው መለወጥ አለባቸው ቢባልም የአለዋወጣቸው ሁኔታና ቅደም ተከተል እንዴት ነው ? ።

ታሪክ ደጋግሞ እንዳሳየው በቅድሚያ ማደግና መሻሻል የሚጀምሩት የምርት ኃይሎች ማለትም የመሣሪያዎች ጥራትና የዕውቀት ማደግን የሚመለከቱ ለውጦች ናቸው ። ግን የመሣሪያዎች መሻሻልም ቢሆን የሰው ዕውቀት መዳበር ውጤት ነው ። የመሣሪያዎች መራቀቅና የሰው ዕውቀት እየዳበረ መሔድ የግድ በሰዎች መካከል የነበረውን ግንኙነት እየለወጠው ይሄዳል ። የምርት ኃይሎች እየተሻሻሉ ሲሄዱ የምርት ግንኙነቶችም መሻሻል አለባቸው ። አብረው ካልተሻሻሉ የሥርዓቱን እድገት ይገቱታል ። ልዩነቱም እየጐላ ሲሔድ የምርት ኃይሎች እንኳን ሊያድጉ ይቅርና ያሉትም በወጉ አይሠራባቸውም ። ይባክናሉ ። ኅብረተሰቡም በሙሉ ይጐዳል ። አዲስና የተሻሻለ ግንኙነት ቢፈጠር የሚያመቻቸውና ስለዚህም የምርት ኃይሎችን ማደግና መሻሻል የሚፈልጉት ተራማጅ ኃይሎች /በአንድ በኩል ሰልፋቸውን ያሳምራሉ ። በሌላ በኩል ደግሞ ያለው ያረጀውና ያፈጀው የምርት ግንኙነት ለነሱ ስለሚያመች እንዳይለወጥ የሚታገሉና በዚህም የምርት ኃይሎችን እድገት የሚገቱ አድኃሪ ኃይሎች ይሰለፋሉ ። የግድ ወደፊት መግፋት ፣ መሻሻልና ማደግ ባለባቸው የምርት ኃይሎችና ባሉበት ለመቆም በሚፍጨረጨሩት የምርት ግንኙነቶች መሐከል ያለው ቅራኔና ትግል እየከረረና እየተፋፋመ ይሄዳል ። ባዲሶቹ የምርት ኃይሎችና በአሮጌው የምርት ግንኙነት መሐከል ተጻራሪ እየሆነ የመጣው ቅራኔ ይፈነዳል ።

ይህ ቅራኔ ደግሞ ያጋጣሚ ነገር አይደለም ። የምርት ኃይሎች በጣም በፍጥነትና ባለማቋረጥ ተንቀሳቃሾ ናቸው ። የምርት ኃይሎች በአንድ ስልተ ምርት ውስጥ እንኳን ብዙ መለዋወጥና ማደግ ሲያሳይ የምርት ግንኙነቶች ግን እጅግ ዝግ ባለ ርምጃ ብቻ ነው የሚጓዙት ለምሳሌ በካፒታሊዝም ሥርዓት ውስጥ የምርት ኃይሎች ከዛሬ መቶ ዓመት ጋር እንኳን ሲነጻጸሩ እጅግ ወደፊት ተራምደዋል ። ተራቀዋል ። የምርት ግንኙነቶች ግን አብረው አልተሻሻሉም ።

ይህም ማለት እርግጥም የአንድን ኅብረተሰብ ስልተምርት የሚወስኑት የምርት ኃይሎችና የምርት ግንኙነቶች በአንድነት ተዋሕደው ቢሆንም የምርት ግንኙነቶችን በልማድ በመደብ ጥቅምና በፍልስፍና . . . የሚወሰኑም በመሆናቸው ከምርት ኃይሎች ጋር ሲነጻጸሩ ወግ አጥባቂነት ያጠቃቸዋል ። እንደዚህም በመሆኑ በፍጥነት ከሚያድጉት የምርት ኃይሎች ጋር ግጭት ይኖራቸዋል ። በዚህም ግጭት መከረር የተነሣ በኅብረተሰቡ ውስጥ የቀድሞውን የምርት ግንኙነት ሰባብሮ በሰዎች መሐከል አዲስና የተሻለ ርምጃን የሚያግዝ አብዮት አስፈላጊነት እየጐላ ይታያል ። እስቲ እንግዲህ ይህን ትግል እንዴትስ አብዮት እንደሚያስከትል በተጨባጭ ሁኔታ እንመልከት ።

የኅብረተሰብ ታሪክ ማለት የልዩ ልዩ ስልተ ምርቶች መሻሻልና መከታተል ታሪክ ነው ብለናል ። በዚህ አንጻር ስንሄድ እንግዲህ በሰው ዘር ታሪክ ሲታይ አምስት ዓይነት ስልተምርቶች ይገኛሉ ። እነሱም የጥንት የጋርዮሽ ዘመን ፣ የባሪያ ዘመን ፣ የፊውዳል ዘመን ፣ የከበርቴ ዘመን ፣ የሶሻሊዝም ዘመን ስልተምርቶች ናቸው ።

(ይቀጥላል)